**ነሓሴ 2002 ዓ.ም**

## የኢሮብ ወጣቶችን ከቀያቸው የማፍለስ ንግድ ባስቸኳይ ይቁም

በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግሮች ምክንያት በትውልድ ቀያቸው ኑሮአቸውን ለመቀጠል የሚያስችል ብሩህ ተስፋ ለማየት ያልታደሉት በርካታ የኢሮብ ወጣቶች ተወልደው ያደጉበት ቀያቸውም ሆነ ውድ ሀገራቸውን እንደ ሌሎቹ በርካታ የኢትዮጵያ ወጣቶች እየለቀቁ መሰደድ ከተስተዋለ ሰንበትበት ብሏል። ይህ የኢሮብ ወጣቶች ሆነ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ወጣቶች በብዛት የመሰደድ ክስተት የተጀመረው በደርግ አገዛዝ ዘመን ሲሆን፤ በወቅቱ እንደ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ወጣቶች የኢሮብ ወጣቶችም ይሰደዱበት የነበረው መሰረታዊ ምክንያት የደርግን አገዛዝ ምህረት አልባ እርምጃዎቹን ለመሸሸ ነበር። ባሳለፍናቸው 20 ዓመታት የኢህአዴግ አገዛዝ ዘመንም እነዛ ለኢሮብ ወጣቶች መሰደድ ምክንያት የነበሩ ሁኔታዎች ባለመወገዳቸው የሚያሰድዳቸው መሠረታዊ መንስኤ በይዘትም ሆነ በዓይነት በደርግ አገዛዝ ወቅት ከነበረው በምንም መልኩ አይለይም። በመሆኑም ዛሬም አጠቃላይ የኢትዮጵያ ወጣቶች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው በተለየ መንገድ እንደተረገጡ ነው። በተለይ የኢሮብ ወጣቶች ሁኔታን ስንመለከት ደግሞ፤ በአከባቢው ለብዙ ዓመታት ያለማቋረጥ የተከሰተው ድርቅ ሌላው ተጨማሪ ምክንያት ነው ማለት ይቻላል።

በመሆኑም፤ ዛሬም የኢሮብ ወጣቶች በአከባቢው ለመኖር የሚያስችል ምንም ዓይንት ብሩህ ተስፋ ማየት አልቻሉም። ስለሆነም በርካታ የኢሮብ ወጣቶች በደርግ አገዛዝ ጊዜ ከነበረው ቁጥር በበለጠ ደረጃ የተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም አከባቢውን እየለቀቁ በመፍለስ ላይ ናቸው። ይህ የወጣቶች ፍልሰት በኢሮብ አናሳ ብሄረሰብ ህልውና መቀጠል ላይ ያለው አሉታዊ እንደምታ አሌ የማይባል ነው። በተለይ አሁን ወጣቶቹ እየወሰዱት ያለው፤ በህይወታቸው ላይ ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትሉ የምችሉ የስደት እርምጃዎችን ስንመለከት ደግሞ አስቸኳይ የእርምት እርምጃ ይወሰድበት ዘንድ የሚመለከተውን ሁሉ ማሳሰብ አንገብጋቢና ወቅታዊ ሆኖ አግኝተነዋል።

ዛሬ የኢሮብ ወጣቶች በቀያቸው በተንሰራፋው ብልሹ፣ ኢ-ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርና የተፈጥሮ መዛባት ባስከተላቸው ችግሮች ምክንያት በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ አንድነትና ለኢሮብ ብሄረሰብ ህልውና ከፍተኛ አደጋ ወደሆነው ወደ ሻዕቢያ ሲኮበልሉም እየተስተዋለ ነው። ሌላው ይህን መግለጫ ለማውጣት ያነሳሳን መሰረታዊ ምክንያት የኢሮብ ወጣቶች ፍልሰት በተደራጁ ገንዘብ አምላኪ ወንጀለኞች በመካሄድ ላይ ስለሚገኝ ነው። ዛሬ "ሕግና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት" አለበት በምንባልበት አገር ውስጥ የተደራጁ ወንጀለኞች የቅብብሎሽ የእዝ ሰንሰለታቸውን ከኢሮብ መሬት እስከ እስራኤል ድንበር ድረስ በመዘርጋት፤ የወጣቶችን ልብ እያማለሉ፣ የገንዘብ ፍላጎቻቸውን ብቻ ለማርካት በወጣቶቹ ህይወት እየነገዱ እንደሆነ በግልጽ እየተመለከትን ነው።

ይህንን በወጣቶቹ ህይወት በሚነግዱት ወንጀለኛ ቡድኖች የሚከናወነው አስነዋሪ ተግባር እየተፈጸመ ያለው በኢሮብ ወጣቶች ላይ ብቻ ሳይሆን በመላው ኢትዮጵያ ወጣቶች ላይም

እንደሆነ ውስጥ አዋቂ ምንጮች እየጠቆሙን ነው። እነዚህ ወንጀለኛ ቡድኖች ከሚያጠምዱዋቸው ወጣቶች መካከል ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ልጆችም በብዛት እንደሚገኙበት ይታወቃል። በፆታም ቢሆን ወንድና ሴት እንደማይለዩ ይታውቃል። ገንዘብ መክፈል ይችላል ተብሎ የሚገመት ሁሉ ለስደት እንደሚመለመልም ይነገራል። ወጣቶቹ አከባቢያቸውን ለቀው ቢሰደዱ ስራ እንደልብ እንደሚያገኙና በምድረ_እስራኤል ምድራዊ ገነት እንደሚጠብቃቸውም ይሰበክላቸዋል። በመሆኑም፤ በትውልድ ቦታቸው ላይ በሰላም ሠርቶ የመኖር ተስፋ የተመናመነባቸው ወጣቶችና ሕፃናት የነዚህ አውሬዎች ጭዳ በመሆን ላይ ናቸው። ቡድኖቹ ወጣቶቹን ከየአከባቢው እያማለሉ ካሰባሰቡ በኋላ፤ ለጉዞ በሚጠቀሙባቸው መሥመሮች ላይ የማስተናገጃ ቦታዎችን በማዘጋጀት ካንዱ ጣቢያ ወደ ሌላው እየተቀባበሉ በማጓጓዝ ወጣቶቹ ለስንቅ የቋጠሩዋትን ሳንቲም በየመንገዱ ይቀራመቱዋታል። ለስደት የሚመለመሉት ወጣቶች ሰሜን ኢትዮጵያን፤ ሱዳንንና ግብፅን አቋርጠው እንዲጓዙ በማድረግ በሲናይ በረሃ የማሰባሰብያ ካምፖች አዘጋጅተው ለሚጠብቁ ለተለያዩ ጨካኝ ቡድኖች ያስረክቧቸዋል።

እነዚህ የኢሮብ ወጣቶችን አማልለው እያሰባሰቡ የሚያጓጉዙ ወንጀለኛ ቡድኖች፤ ወጣቶቹ ሲናይ በረሃ የሚገኙትን ካምፖች እስኪደርሱ ድረስ ወደ እስራኤል ለመግባት የሚከፈል ገንዘብ እንዳለ እንኳ አይነግሩዋቸውም። በሕይወት ተርፈው ወደ እስራኤል የመሻገር ዕድላቸውን ለመሞከር የታጋች ወጣቶችን ቤተሰቦች የገንዘብና የሥነ-አእምሮ ችግር ያስከተለ በብዙ ሺ የሚቍጠርና የአሜሪካን ዶላር መክፈል እንዳለባቸው የሚነገራቸው እዛው ሲናይ በረሃ ሲደርሱ በሚረከቧቸው ጨካኝ የወንጀለኛ ቡድኖች ነው። ይህንን ሃቅ ደግሞ ዘመድ አዝማድን አስጨንቀው መክፍል ያላባቸውን ገንዘብ ከፍለው እስራኤል ለመግባት ከቻሉ ወጣቶች ለማረጋገጥ ይቻላል።

እነዚህ በሲናይ በረሃ የሚገኙ ቡድኖች ለዚህ አሰቃቂ ተግባር በደንብ የተዘጋጁና የተደራጁ በመሆናቸው ወጣቶቹ ከላይ የተጠቀሰውን የአሜሪካን ዶላር ባስቸኳይ እንዲከፍሉ አካላዊና ስነ-አእምሮአዊ ጫና ያደርሱባቸዋል። የተጨነቁ ወጣቶች ለህይወታቸው ማዳኛ የተጠየቁትን ገንዘብ እንዲከፈልላቸው በአመሪካ፤ በአውሮፖ፣ በዓረብ አገሮች እንዲሁም ሀገርቤት ወዳሉት ዘመዶቻቸው በመደወል እሪ እንዲሉ የተለያዩ የማሰቃያ ዘዴዎችን በመጠቀም ያስገድዷቸዋል። ለዚህ ተግባርም፤ እነዚህ ወንጀለኛ ቡድኖቹ ታጋቾቻቸው ከዘመድ አዝማድ ጋር በመገናኘት እንዲከፍሉ የሚጠየቁትን ዶላር እንዲያሰባስቡ ለማስቻል እንዲያመቻቸው የተለፎን መስመሮችን አመቻችተው ይጠብቁዋቸዋል። በዚህ መልክ የማስለቀቅያ ገንዘብ (Ransom) ከተረከቡ በኋላ ይለቋቸዋል፣ በዚህም የስንቱ ቤተሰብ ኑሮ አመሰቃቅለዋል። የተጠየቀውን የገንዘብ መጠን መክፈል ያልቻለ ታጋችም እጣ ፈንታው እዛው በሲናይ በረሃ መቅረት ይሆናል።

እነዚህ ወጣቶች ከኢሮብ መሬት (የትግራይ ምስራቃዊ ጫፍ) ተነስተው ትግራይን አቋርጠው ሲጓዙ የሚያልፉባቸው ቦታዎች ሁሉ የመንግስት አስተዳደርና የተለያዩ የመንግስት የጸጥታ መዋቅሮች ያለባቸው አከባቢዎች መሆን፣ ዛሬ የኢህአዴግ መንግስት "ዴሞክራሲና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በሽበሽ" ነው እያለን ባለበት ባሁኑ ወቅት ወጣቶቹ ውድ ቀያቸውንና ሀገራቸውን እየለቀቁ ለመሰደድ መገደድ ለምን ይሆን? የሚለው ጥያቄ እያንዳንዱ ወገን

ሊጠይቀውና ተገቢ መልስ ሊያገኝለት የሚገባ መሰረታዊ ጥያቄ ነው። በኛ እምነት መንግሥትና የመንግስት ተቋማት ባለበት ሀገር እንዲህ ዓይነት የሀገሪቷ መጻኢ ተስፋ የሆኑትን ወጣቶችን የሚያፈልስ ንግድ በነፍሰበላ ዘራፊዎች ሲካሄድ ማየትና መስማት አሳፋሪም፤ አሳዛኝም ሆኖ አግኝተነዋል።

እስካሁን ድረስ ባለን መረጃ ከኢሮብ አናሳ ብሄረ-ሰብ ብቻ በነዚህ ዘራፊ ወንጀለኛ ቡድኖች ወጥመድ ውስጥ የገቡት ወጣቶች ቁጥር በብዙ ሞቶዎች የሚቆጠር ነው። ከነዚህም ውስጥ በተለያየ ጊዜ በተደረጉ ጉዞዎች በበረሀ ውስጥ በውኃ ጥምና ረሃብ እንዲሁም በተለያዩ በሽታዎች ሕይወታቸውን ያጡ ወጣቶች መኖራቸው ይታወቃል። አሁንም ቢሆን ብዙዎች በግብፅና በእሥራኤል እሥርቤቶች እንዲሁም በነዚህ ማፊያዎች ቁጥጥር ስር በሚገኙ ልዩ ልዩ ካምፖች ውስጥ እየተሰቃዩ መሆናቸውን አውቀናል።

ስለዚህ ይህ አጠቃላይ የወጣቶች ፍልሰት እንዲቆም፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች በአንድነት ማለትም የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ፣ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶችና እንዲሁም ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው መንግስታት በጋራ ይህንን የሰው ንግድ በአስቸኳይ እንዲቆም አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገር ለሚገኙ የኢሮብ ብሄረሰብ አባላት ደግሞ፣

1. ወጣቱ ትውልድ ወደዚህ አደገኛ ሁኔታ ራሱን እንዳያስገባ በተገኘ አጋጣሚ ሁሉ መተላለፍ ያለበትን መልእክት እንዲያስተላልፉ
2. በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የኢትዮጵያ መንግስት ባለስልጣናትን፣ ይህን የወጣቶች ፍልሰት ይቆም ዘንድ አስፈላጊ እርምጃ እንዲወስዱ መጠየቅ
3. ዓቅም በፈቀደ ሁሉ ከሰብአዊ መብት ተሟጓች ድርጅቶችና፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በመተባበር ይህ የወጣቶች ፍልሰት እንዲቆም አበክሮ መስራት፣
4. የኢትዮጵያ መንግስት ለነዚህ የወጣቶች ፍልሰት መንስኤ የሆኑ መሰረታዊ ችግሮች ከብሄረሰቡ ሽማግሌዎች፣ ከራሳቸው ከወጣቶቹና በጉዳዩ ላይ እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች ጋር በመመካከር ይህ የወጣቶቹ ፍልሰት የሚቆመበት መንገድ ባስቸኳይ እንዲፈለግ፤ እነዚህ ወጣቶችን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በማስኮብልለ ተግባር ላይ ተሰማርተው የሚገኙትን ቡድኖች ታድነው ለፍርድ እንዲያቀርብ፤ አስፈላጊውን ግፊት ሁሉ በጋራ እንድናደርግ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

በተቸገሩ ወጣቶች ላይ መነገድ ባስቸኳይ ይቁም!!!

ሁኔታው ያሳሰበን የብሔረ-ሰቡ ተወላጆች።